# የነፃነት እጦት የወለደው ፌዴራሊዝም

ኑርዘላለም ከአዳማ

በመጪው ግንቦት ለሚካሄደው ምርጫ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ ከእነዚህ መካከል በምርጫው ላይ የሚሣተፍ ፓርቲዎች የአቋም ክርክር ይገኝበታል፡፡ እስከአሁን ‹‹መድብለ ፓርቲ ሥርአት ምርጫና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ›› እና ‹‹የፌዴራሊዝም ሥርአት በኢትዮጵያ›› "መልካም አስተዳደር፣ ሰብዓዊ መብትና የሕግ የበላይነት" በሚሉ ሦስት አጀንዳዎች ላይ ፓርቲዎች አቋማቸውን አሳውቀውናል።

በእነዚህ ክርክሮች ላይ ፓርቲዎቹ ያቀረቡዋቸው አቋሞቻቸው የመራጩን ሕዝብ ድምጽ ማግኘትና አለማግኘት ላይ ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ በሌላ አነጋገር የመንግስት ሥልጣን መረከብ መቻል ወይም ያለመቻል የሚወሰነው በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ በሚይዙት አቋም ነው፡፡ መራጮች የየትኛው ፓርቲ አቋም የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ፣ የሕዝቡን ፍላጎት ያገናዘበ እንደሆነ፣ የአገሪቱን ዘላቂ ሕልውና በሚያረጋግጥ አኳኋን ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችሉ ለመለየት በቂ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፤ ወይም እንዲኖረው ይጠበቃል፡፡በመሆኑም በአንድ የጋዜጣ ጽሁፍ ማስተናገድ የሚቻለውን ያህል በተለይ መራጩን ሕዝብ የጠራ እይታ እንዲኖረው ሊያደርገው በሚችል መንገድ ቀርቧል ያልኩትንና ለአገሪቱ ዘላቂ ሕልውና ወሣኝ ነው ብዬ ያመንኩበትን መቃኘት ወድጃለሁ፡፡ ለዛሬ የካቲት 14 እና 15 ለሕዝብ የቀረበው ‹‹ፌደራላዊ ሥርአት በኢትዮጵያ›› በሚል አጀንዳ ላይ በአምስት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ኢህአዴግ አንድነት መድረክ ኢዴፓ፣ ቅንጅት፣ ኢራፓ መሀከል የተካሄደው ክርክር ላይ ፓርቲዎቹ ይዘው የቀረቡት አቋም ላይ አተኩራለሁ፡፡

በዚህ ‹‹ፌደራሊዝም በኢትዮጵያ›› የሚል አጀንዳ ላይ አምስቱም ፓርቲዎች ባቀረቡዋቸው አቋሞች የፌዴራሊዝም ሥርዓት እንደሚቀበሉ ገልጸዋል። በአወቃቀር ላይ ግን የተለያየ አቋም እንዳላቸው ነው ያሳወቁን፡፡ የአቋም

ልዩነታቸውን በአጠቃላይ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ ኢ.ደ.ፓ፣ ቅንጅትና ኢ.ራ.ፓ በአንድ ወገን የፌደራል አወቃቀሩ ብሔርን መሠረት ያደረገ ሣይሆን መልከአ ምድራዊ መሆን ይገባዋል የሚል አቋም ሲይዙ፤ በዶ/ር መራራ ጉዲናና ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ የተወከለው የመድረክ ፓርቲ እና የኢሕአዴግ አቋም ብሔርን መሠረት ያደረገ አወቃቀርን የሚደግፍ ነው፡፡ መድረክ በተጨማሪ እንደክልል መንግስት የተሠጠው ሥልጣን አንሷል በሚልና ሌሎች በክልላዊ መንግስትነት መዋቀር ያለባቸው ብሔሮች አሉ በሚል አቋም ተለይቷል፡፡

ፓርቲዎቹ የያዙት አቋም ተገቢና ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጥልናል ያሉዋቸውን የመከራከሪያ ሀሣቦችም (argument) አቅርበዋል፡፡

በዚህ ጽሁፍ በኢ.ዴ.ፓ፣ ቅንጅትና ኢ.ራ.ፓ የቀረበውን የአገሪቱ የፌዴራል አወቃቀር ብሔርን መሠረት ያደረገ ሣይሆን መልክዐ ምድራዊ መሆን አለበት የሚል አቋም ላይ የቀረቡ መከራከሪያ ሐሣቦች ላይ አተኩራለሁ፡፡ በእነዚህ ፓርቲዎች የአቋማቸውን ተገቢነትና አስፈላጊነት ያስረዳልናል ብለው ያቀረቡት መከራከሪያ አቋም ጠቅለል ባለመልኩ፣ የፌደራሉ ክልላዊ መንግስታት ብሔርን መሠረት ያደረገ መሆኑ በተለይ ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 39 ላይ "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው" በሚል ከሠፈረው ድንጋጌ ጋር በማያያዝ አገሪቱን ለመገነጣጠል አደጋ ያጋልጣል የሚል ነው፡፡

በዚህ አቋምና የአቋሙን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በቀረቡት መከራከሪያዎች እንደተባለው አሁን ያለው ብሔር ተኮል የፌዴራል አወቃቀር አገሪቱን ለመገንጣጠል አደጋ ያጋልጣል ወይ? የሚለውን እና በሌላ በኩል እንደ አማራጭ የቀረበ መልከምድራዊ  አወቃቀር ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ትክክለኛና ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ወይ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ

ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የአገሪቱን ታሪካዊና ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ማየት ይሻል።

ያለፉት ሁለት ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያን ታሪክ በሁለት ዋና አንጓዎች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው እስከ19ነኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ የነበረው ሲሆን፣ ሁለተኛው ከ19ነኛው ክፍለ ዘመን የኢፌዴሪ መንግሥት እስከተመሠረተበት 1980ዎቹ አጋማሽ ያለው ነው፡፡

እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ፣ ሠሜናዊው የአገሪቱ ክፍል የተወሠኑ ጊዜያት የመንግሥስት ሥልጣን በየአካባቢው መሣፍንት የተበታተነበት ሁኔታ ቢኖርም በአጠቃላይ ከአንድ ዘመንና ስርወ መንግስት በሚመዘዝ ዘውዳዊ የመንግስት ሥርአት ሲተዳደር የነበረበትን ሁኔታ እናገኛለን፡፡ በዚሁ የታሪክ አንጓ ውሰጥ የአሁኗን ኢትዮትያ ደቡባዊ ምሥራቃዊና ምእራባዊ አካባቢዎች የሚኖሩ ብሔር ብሔሠቦች በየራሣቸው የመንግስት ሥርአት፣ በንጉሣዊም ጭምር በተበትተነ ሁኔታ ራሣቸውን ያስተዳድሩ ነበር፡፡

19ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ ላይ ሰሜናዊው ዘውዳዊ ንጉሣዊ የመንግሥት ሥርዓት በማዕከላዊ፣ ደቡባዊ ፣ ምሥራቃዊና ምዕራባዊ አካባቢዎች በየራሣቸው የመንግስት ሥርአት ሲተዳደሩ የቆዩትን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከፊሉን በዲፕሎማሲ በዚህ ያልተቻለውን በኃይል ተቆጣጥሮ አሁን ያለውን የኢትዮጵያ ወሠን በመፍጠር በአሐዳዊ የመንግስት ሥርዓት ማስተዳደር ጀመረ፡፡ የአስተዳደሩ መዋቅር የአሀዳዊውን ንጉሣዊ ሥርአት መርሕና ፍላጎት በማስጠበቅ ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ የአስተዳደሩ ግዛቶች፣ ጠቅላይ ግዛቶች፣ አውራጃና ወረዳዎች ሁለትና ከዚያ በላይ የተለየየ መገለጫዎች ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ… ያላቸውን ብሔሮች ብሔረሠቦችና ሕዝቦች በአንድ ላይ በመጨፍለቅ - በሌላ በኩል አንድን ብሔር ብሔረሠብ

ሁለትና ከዚያም በላይ በበጣጠሰ ሁኔታ የተዋቀረ ነበረ፡፡በዚህ ሁኔታ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው የእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ አባላት ከራሣቸው ቋንቋ ውጭ መግባቢያ ቋንቋ የማይችሉና በየራሳቸው ባህል መሰረት የሚኖሩ ቢሆንም የዘውዳዊው መንግሥት ብሔር ቋንቋ የመንግሥት የሥራ ቋንቋና የትምህርት መስጫ ቋንቋ መሆኑ በሕግ ተደነገገ፡፡ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ፣ ሕዝቦች በብሔራዊ ማንነታቸው ህጋዊ እውቅና ከመነፈጉ ጋር ተያይዞ፣ ኢኮኖሚያዊ ጭቆናም ተፈፅሞባቸዋል፡፡

ፊውዳላዊው የዘውድ ሥርአት ወደራሱ ግዛት በጠቀለለው አካባቢ የሚኖሩ የየብሔር ብሔረሰቡ ሕዝብ ዘር ማንዘሩ ዝንተ አለም ሠፍሮበት እያለማ የኖረበትን መሬት ባለይዞታነት የመጠቀም መብት ተነፍጎ ለገባርነት ተዳርጓል፡፡በወቅቱ የኢትዮፕያ ብሄር ብሄረሰቦች ይህንን መብትና ነጻነታቸውን የነጠቃቸወን ዘውዳዊ ሥርዓት ከላያቸው ላይ በማንሳት ነፃነታቸውን ማስከበር ቀላል ያልነበረ ቢሆንም የግፍ አገዛዙን በፀጋ ግን አልተቀበሉትም፡፡ የብሔራዊና ኢኮኖሚያዊ መብትና ነፃነት ጥያቄዎችን አንስተዋል፡፡ በተለይ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለያዩ መነሻዎች ባልተደራጀ መልኩ ግብታዊ የአርሶ አደር አመፆች የተካሄድበት ሁኔታ ነበር፡፡ በኋላም ይህ የብሔራዊና ኢኮኖሚያዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ፣ መርሕ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ጥያቄ መልክ መያዝ ጀመረ፡፡በተለይ ከ50ዎቹ ማገባደጃ በኋላ ጎልቶ የወጣው ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ ነበር፡፡ ይህ ከብሔራዊ ጭቆና ጋር የተያያዘ ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ የቀሰቀሰው ህዝባዊ አመፅ በ1966 ዘውዳዊውን ሥርአት ለውድቀት ያበቃ ዋንኛው ምክንያት ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ የወደቀውን ዘውዳዊውን የመንግስት ሥርአት የተካው ወታደራዊ መንግስት ከአገሪቱ ህዝብ 90 በመቶ ያህል የሚወሰነውን አርሶ አደር ለሚመለከተው የኢኮኖሚ በመሬት ለአራሹ ጥያቄ ምላሽ ሰጠ፡፡ ከዚሁ ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ ጋር የማይነጣጠለውና ተመሣሣይ መነሻ የነበረውን ብሔራዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ ግን ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ ሣይሆን ቀርቷል፡፡

ከ1966 በኋላ ባሉት አንድ ተኩል አስርት አመታት ውስጥ በርካታ ብሔርና ብሔረሠቦች በነፃነት ግንባሮች ተደራጅተው የትጥቅ ትግል ማካሄድ ጀመሩ፡፡ ወታደራዊውን የደርግ - ኢሠፓ የመንግሥት ሥርዓት ለውድቀት ያበቃውም ይሔው በየአቅጣጫው የተቀጣጠለበት የትጥቅ ትግል ነው፡፡ በ1983 ዓ.ም. ከወታደራዊው የደርግ ኢሠፓ መንግስት ውድቀት ጥቂት ቀናት በፊት ፕሬዚደንቱ መንግስቱ ኃ/ማርያም ባረጉት የመጨረሻ ንግግራቸው፣ ከ20 በላይ በብሔር ብሔረሠብ የተደራጁ የነፃነት ግንባሮች የትጥቅ ትግል ያካሂዱ እንደነበር በይፋ ማመናቸውን ለዚህ አስረጂነት መጥቀስ ይቻላል።

ከ1983 ሰኔ-1987 የቆየው የሽግግር መንግሥቱ ቻርተርና በ1987 የፀደቀው የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉአላዊ ሥልጣን ባለቤቶች መሆናቸውን የደነገገውም ለዚህ ነው። ሰብዓዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መብትና ነፃነት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ራሣቸውን በራሣቸው የማስተዳደር መብታቸው መከበሩን ማረጋገጥ እንዲችሉ የፌዴራሉ አወቃቀር፣ በብሔር ላይ የተመሠረተ ክልላዊ መንግስት እንዲሆን ያስፈልገው ለዚህ ነው፡፡ ከዚያ ቀደም ተነስቶ የነበረውና የትጥቅ ትግል በመቀስቀስ፣ የወታደራዊውን ደርግ ኢሠፓ መንግሥት ለመጣል ያበቃው ዋነኛ ጥያቄ የብሔራዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ ሥለነበር ለዚህ ምላሽ አለመስጠት ከሠብአዊ መብት መርሕ አኳያ ኢ-ፍትሐዊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የትጥቅ ትግሉ መቀጠል አይቀሬ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ምርምር አያስፈልገውም፡፡

አሁን ሦስቱ ፓርቲዎች - ኢዴፓ፣ ቅንጅት፣ ኢራፓ በፓርቲዎች የአቋም ክርክር ላይ ያቀረቡት ‹‹ መልከአምድራዊ ፌዴራላዊ አወቃቀር፣ ቀደም ሲል የብሔራዊ መብት የትጥቅ ትግል እንዲቀሠቀስ ምክኒያት የሆኑ መንግስታት የአስተዳደር ሥርአት ደግሞ ከመመለስ የተለየ አይደለም፡፡ የዚህ አቋም ተግባራዊነት አንድን ብሔር ወይም ብሔረሰብ ሁለትና ሦስት ቦታ በመበጣጠስ፣ ሁለትና ከዚያ በላይ በአንድ አስተዳደር ሥር በመደባለቅ በቋንቋቸው የመጠቀም እድላቸውን፣ ባህላቸውን የማዳበር አቅማቸውን

ያዳክመዋል፣ ወይም ይህን እድልንና አቅም ፈፅሞ ሊያሳጣቸው ይችላል፡፡ በአጠቃላይ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የኢትዮጵያ ብሄሮቸ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ግብር ከፍለው በሚኖሩበት አገር የሚችሉት ብቸኛና የራሳቸው መግባቢያ ቋንቋ፣ ፍትሕን ጨምሮ ሌሎች መንግስታዊ አገልግሎቶችን የማግኘት ልጆታቸቸውን የማስተማር ወዘተ… ግለሠባዊና የቡድን መብታቸውን የሚጥስ ነው፡፡ ይህን መሠረታዊ የግለሠብና የቡድን መብት ያልተከበረበት ብሔር ወይም ብሔረሰብ በሚኖርበት ወሠን ውስጥ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር የሚያስችለው ነፃ ግዛት ለመመሥረት ለብሔራዊ ነፃነት የትጥቅ ትግል እንዲያካሂድ የሚያስገድደውን ሁኔታ ስለሚፈጥር የአሁኗን ኢትዮጵያ ግልጽና ቅርብ ለሆነ የመገነጣጠል አደጋ ያጋልጣታል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አወቃቀር ከኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 39 ላይ ከተፈቀደው እስከ መገንጠል የዘለቀ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት አገሪቷን ይበታትናታል የሚለው ሥጋትም፣ የብሔራዊ ነፃነትን መርሕ ያላገናዘበና መሠረተ ቢስ ሥጋት ነው፡፡ በቅድሚያ አንድ ብሔር ወይም ብሄረሠብ የሚያነሳው የመገንጠል ጥያቄ መድረሻው መገንጠል አይደለም፡፡ መድረሻው ብሔራዊ መብትና ነፃነት ካልተከበረበት ሥርአት ተላቀው ራሣቸውን በራሣቸው የሚያሰተዳድሩበት ነፃ ግዛት መመስረት ነው፡፡ በርካታ ብሔር፣ ብሔረሠቦች ብሔራዊ መብታቸውና ነፃነታቸው ተከብሮ ራሣቸውን በራሣቸው እያስተዳደሩ በአንድ ፌደራላዊ የመንግስት ሥርአት የመኖር መብታቸው ከተረጋገጠ የመገንጠል ጥያቄ እንዲያነሡ የሚያስገድድ ምንም ቅድመ ሁኔታ አይኖርም፡፡ ይህ ቅድመ ሁኔታ ከሌለ ጉዳዩ የሕዝብ ጥያቄ ሆኖ ሊነሳ አይችልም፡፡ የሕዝብ ጥያቄ ሆኖ የመነሳት ዕድል ከሌለው ደግሞ በጥቂት የብሔረሰብ ወይም ብሄር አባላት ቡድን ቢነሳ እንኳን በተለይ የመገንጠል ጥያቄው ሕገ-መንግሥታዊ አካሄድ ተበጅቶለት በሕዝብ ውሳኔ የሚፀናበት ሥርዓት ባለበት ሁኔታ የትም አይደርስም፡፡

በመሆኑም በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 39 ላይ የሠፈረው እስከመገንጠል የዘለቀው መብት፣ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ መብትና

ነፃነታቸው መከበር ዋስትና የሚሠጥ እንጂ ለመገንጠል የሚያነሣሣ አይደለም፡፡ መብትና ነፃነታቸው ካለተከበረ፣ እስከመገንጠል የዘለቀ መብት የሚሰጥ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ባይኖርም፣ የመገንጠል ጥያቄ ከማስነሣት፣ ለዚህ ተግባራዊነት የትጥቅ ትግል ከማካሄድ አይገድባቸውም፡፡ ምናልባት ልዩነቱ ተገንጥሎ ነፃ መንግስት የመመስረቱን ሒደት ሠላማዊ ያልሆነ በጦርነት የሚከናወን እንዲሆን ማድረጉ እንጂ፡፡

በመሆኑም የኢፌዴሪን ፌዴራላዊ፣ አወቃቀርና የሕገ-መንግሥቱን አንቀፅ 39 የሚቃወሙ ወገኖች አቋም ምናልባት የቀድሞዎቹ የመንግስት ሥርአቶች አመለካከት ሠለባ ከሆኑ እጅግ በጣም ጥቂት ኢትዮጵያውያን ካልሆነ በስተቀር፣ ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው የተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሠብና ሕዝብ አባላት በሆኑ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለውም ግልጽ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ይህን አቋም እንደፓርቲ አቋም ይዘው ወደምርጫ ለሚገቡ ፓርቲዎች የመንግስት ሥልጣን ለመረከብ ወይም ለመጋራት የሚያስችል የሕዝብ ድምጽ ማግኘት አያስችላቸውም፡፡ፓርቲዎቹ ይህን አቋም እንዲይዙ ያነሳሳቸው የተለያየ ምክንያት ሊኖር ይችላል፡፡ አንድ፣ የብሔር ብሔረሰብ መብት እውቅና ነፍገው የነበሩት የቀድሞዎቹ ሁለት የመንግሥት ሥርዓቶች አመለካከት አራማጅና ናፋቂ መሆን፤ ሁለት እነዚህ ሥርዓቶች ለአንድ ክፍለ ዘመን ያካሄዱት ከሰባ በላይ የየራሳቸው መገለጫ ያላቸውን የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሶቦች በአንድ ብሔራዊ ማንነት የመዋጥ ዘመቻ ሰለባ መሆን፤ ሦስት አሁን ባለው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ከሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች የተለየ እና/ ወይም የተሻለ አቋም ይዘው ለሥልጣን የሚያበቃ የአብላጫ ኢትዮጵያውያንን ድምፅ ማግኘት እንደማይችሉ በመገመት፣ የጥቂት የቀድሞዎቹ ሥርዓቶች አመለካከት ሰለባዎችን ድምፅም ቢሆን ከማግኘት ጥቂት የም/ቤት መቀመጫዎችን በመቋደስ ከውስን እይታ የመነጨ ፍላጎት ሊሆን ይችላል፡፡ እርግጥ የኢትዮጵያን ታሪካዊና ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም የሰብአዊ መብት መርሆች ላይ ካለ የግንዛቤ እጥረት የመነጨ የየዋህነት ስህተት ሊሆንም ይችላል፡፡ ብሔር ብሔረሰብ ላይ የተመሠረተው የአሁኗ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አወቃቀር፣ በአንድ ወገን ፍላጎት

የተሰጠ ሳይሆን ያለፉት የመንግሥት ሥርዓቶች ሲከተሉት የነበረው የፖለቲካ መርህ ያስከተለው የመብትና ነፃነት እጦት የወለደው ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የቀሰቀሰውን የመብትና የነፃነት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ የሰጠ በመሆኑ የአገሪቱን አንድነት ተጠብቆ መኖር ካለበት ያለአማራጭ የሚመረጥ መሆኑ መታሰብ አለበት፡፡